በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች


**መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


***ቦታ፦*** **ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ**

**በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30**

**ጥቅምት ፲፰ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.**

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች

**መግቢያ**

- የመልዕክቱ ጸሐፊ ቅዱስ ጳውሎስ ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን አባቶች እርሱ እንደጻፈው ያምናሉ፡፡
- የጻፈበት ቦታ ቆሮንቶስ ነው፡፡
- በበዓለ ጰንጠቆስጤ ወደ ኢየሩሳሌም የሄዱ መንገደኞች የምስራቹን ወይም በኢየሩሳሌም የሆነውን ዜና ይዘው ወደ አገራቸው ተመልሰው ክርስትናን ለሌሎቹ ሰብከው ነበር፡፡
- በቅዱስ እስጢፋኖስም ሞት ከኢየሩሳሌም ከተበተኑት ክርስቲያኖች መካከል አንዳንዶቹ ወደሮም ሄደው ወንጌሉን ወይም የማዳኑን ምስራች ሰብከው ነበር፡፡
- አስቀድሞ በሮም የሰበከው ቅዱስ ጳውሎስ ሲሆን ቅዱስ ጴጥሮስም በመቀጠል ወደ ሮም ሄዶ ቤተ ክርስቲያንን በዚያ መስርተዋል፡፡
- ከእነዚህም የመጀመሪያዎቹ የሮም ክርስቲያኖች መካከል ከአይሁድ ጋር በቀላውዴዎስ ቄሳር ከሮም የተባረሩት አቂላና ጵርስቅላ የሚገኙ ሲሆን ቅዱስ ጳውሎስ በሁለኛው ጉዞው በቆሮንቶስ አግኝቶአቸዋል፡፡ አቂላና ጵርስቅላም ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር ወደ ኤፌሶን ተጉዘው በዚያ ከሚገኙት ጋር ስለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መስፋት የሚገባውን ሠርተው ወደ ሮም ተመልሰው ቤተ ክርስቲያንን በሮም በምትገኘው ቤታቸው መስርተዋል፡፡ ‹‹በክርስቶስ ኢየሱስ አብረውኝ ለሚሠሩ ለጵርስቅላና ለአቂላ ሰላምታ አቅርቡልኝ፤እነርሱም ስለ ነፍሴ ነፍሳቸውን ለሞት አቀረቡ፥ የአሕዛብም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የሚያመሰግኑአቸው ናቸው እንጂ እኔ ብቻ አይደለሁም፤በቤታቸውም ላለች ቤተ ክርስቲያን ሰላምታ አቅርቡልኝ፡፡ *ሮሜ 16:3-5፡፡*

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች

**መግቢያ**

- በሮም የነበሩ ክርስቲያኖች በእምነታቸውና በመታዘዛቸው የታወቁ ስለነበሩ ቅዱስ ጳውሎስ እምነታቸውና ሥራቸው በብዙዎች ዘንድ የታወቀ መሆኑን ገልጾ አመስግኖ ወደ ነርሱ ሊሄድ የሚናፍቅ መሆኑን ገልጾላቸዋል፡፡
- ወደ ሮም ለመሄድ የናፈቀውም የሮም ክርስቲያኖች በጉዞ እንዲያገለግሉትና እነርሱ በርሱ እርሱም በነርሱ እምነት እንዲበረታቱ ሽቶ ነበር፡፡
- በተለይ አንዳንዶች ከቤተ አይሁድ የመጡ ክርስቲያኖች ሕግን ካልጠበቃችሁና ካልተገረዛችሁ አትድኑም በማለት ከቤተ አሕዛብ የመጡትን ክርስቲያኖች ያስጨንቁ ስለነበር ቅዱስ ጳውሎስ ምላሹን አስጨናቂዎቹ ከዚህ እንዲታቀቡ በመግለጽ የክርስቶስን ወንጌል ትክክለኛ ገጽታ በመልዕክቱ ገለጻላቸው፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ በመልዕክቱ የጌታችን የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ከአይሁድም ሆነ ከአሕዛብ የጎደለውን ሁሉ ሞልቶ የያዘ ሆኖ ሁለቱንም በወንጌሉ የተገለጠው ክርስትና የተካው መሆኑን ጽፏል፡፡
- መልዕክቱ የክርስትናውን ወንጌል የሚያጣምሙትን ጠቅሶ ወንጌሉ በጌታችን በአምላካችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑትን የሚያድን የእግዚአብሔር ኃይል እንደሆነ ገልጧል፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች

## መግቢያ

- ይህም መልዕክት በሮም ለነበረችው ቤተ ክርስቲያን ጥንካሬ ከመስጠቱም በላይ ወንጌሉን በማጣመም ለሚተረጉሙትም ሆነ ወንጌሉ በራሱ በቂ አይደለም ብለው ያምኑ ለነበሩት ለአንዳንዶች የሚሆን ምላሽ የሰጠ ነው፡፡
- መልዕክቱም የጌታችን የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ኃይል የሚያምኑበትን እንዴትና ለምን እንደሚጠብቃቸው ይተነትናል፡፡
- በመልዕክቱ የመጀመሪያው ምዕራፍ አከፋፈል እንደሚከተለው ነው፡-
    - የጸሐፊው ማንነት (1፡1-5)
    - መልዕክቱ የተጻፈላቸው እነማን እንደሆኑ (1፡6-15)
    - ወንጌሉና የስብከታቸው ፍሬ ነገር (1፡16-17)
    - አሕዛብና መዳን ለነርሱ ስለማስፈለጉ ((1፡18-32)
        - እግዚአብሔርን ያላከበሩት በደለኞች (1፡18-23)
        - በበደለኞች የተቆጣ ቅዱስ እግዚአብሔር (24-32)

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 1

**ወደ ሮሜ ሰዎች - ምዕራፍ 1**

- 1፡1 ቅዱስ ጳውሎስ ከሐዋርያት የማንስ በማለት ራሱን በትሕትና ዝቅ አድርጎ ያስተማረን ነው።
- በአይሁድ ዘንድ የታወቀ ሰው መሆኑን በመግለጽ መላ ዘመኑን ሊያገለግል የተጠራ እግዚአብሔርን ፈጽሞ የሚወደደው መሆኑን፣ እግዚአብሔርን ለማገልገል መመረጥ የእውነተኛ ነጻነትን ምንነት የምንገነዘብበት እንደሆነ፣ ለሐዋርያነት መልዕክቱን ለሰዎች እንዲያደርስለት የጠራውም እግዚአብሔር እንደሆነ፣ እግዚአብሔርም ለወንጌሉ ሥራ እንደለየው እንደቀባውና ለዚህም ሥራ እንደወሰነውና ወንጌሉም የአምላካችን የማዳኑ የምሥራች እንደሆነ ጽፎልናል።
- ቅዱስ ጳውሎስ እንደጻፈልን ወንጌሉ የእግዚአብሔር ወንጌል ነው፣ እግዚአብሔር አብ የፈቀደው፣ እግዚአብሔር ወልድ ሰው መሆኑ የተነገረበት ሰውን ያዳነበት፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ላመኑበት የሰው ወገኖች የታደለበት ነው።
- 1፡2 እግዚአብሔር አስቀድሞ ስለመዳናችን በነቢያት ተስፋ ሰጥቶ ቃልም ገብቶ የገለጸልን እንደነበርና ይህም ሰው በሆነ ጊዜ እንደተፈጸመልን ይተረጎማል።
- 1፡3 አምላካችን የተገለጠልን በተለየ አካሉ ከሦስቱ አካላት አንዱ እግዚአብሔር ወልድ ሰው በመሆኑ እንደሆነና፣ እርሱም ከባሕርይ አባቱ ጋር ቀድሞ በኀልውና አንድ የሆነ ‹‹ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ…›› ከእመቤታችን በለበሰው ሥጋ ሰው ሆኖ ተወልዶ ከእርስዋ ወገን በሆነው ንጉሥ ዳዊት የዳዊት ልጅ የሰው ልጅ እንደተባለ እርሱ ግን የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ጻፈልን።

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 1

**ወደ ሮሜ ሰዎች - ምዕራፍ 1**

- 1፡4 ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆኑ ብዙ ምስክሮች ያሉ ቢሆንም ከእነዚህ አንዱ ኃጢአትን ያላደረገ ጌታችን ሞት አያሸንፈውምና በኃይሉ ከሙታን ተለይቶ በሦስተኛው ቀን መነሣቱ ነው።
- ሞት የኃጢአት ደመወዝ ነው፣ እኛን ለማዳን ቃል የገባልን ቅዱስ አምላካችን ግን በቅዱስነቱ ሞትን አሸንፎታል።
- 1፡5 ከእርሱ ከአምላካችን ከኢየሱስ ክርስቶስም የምናስተምርበትን የሐዋርያነት ጸጋ ልናስተምርበት ተቀበልን። ማናቸውንም ነገሮች በእኛ ኃይል አናደርገውምና ስለማደኑ ወንጌል የምናስተምርበትን ጸጋ ሰጠን አለ።
- ወደ ማዳኑ የተጠሩት ሁሉም ናቸውና በታዛዥነት እንዲቀበሉት የሚያገለግሉትም ሁሉ ክብሩን ለራሳቸው ሳይሆን ክብሩ ለሚገባው ለእግዚአብሔር እንዲሰጡ ተናገረ።
- 1፡6 ሁሉም አይሁድም ሆኑ አሕዛብ የማዳኑን ስጦታ እንዲቀበሉ ጻፈላቸው።
- 1፡7 ማንም ሳይጠፋ ሁሉን የሚወድ አምላካችን ሁሉን ለማዳን ወዶ ወደርሱ ይመለሱ ዘንድ እንደጠራቸውና ይህም ፍቅሩ የማይለወጥ ፍቅር እንደሆነ፡ መቀደስ የሚገኘውም ሲታረሙና ሲስተካከሉ በርሱ በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ገልጾ ከሰላምታው ጋር ከኢየሱስ ክርስቶስ የሆነ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን ብሎ ጻፈ።
- ያለ እግዚአብሔር ጸጋ - ጥበቃና ኃይልምንም ልናደርግ አንችልም፤ ሰላምም የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነው

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 1

**ወደ ሮሜ ሰዎች - ምዕራፍ 1**

- ሰው በሕይወቱ የእግዚአብሔር ጸጋና ሰላም ያስፈልገዋል፤ ሰላሙ ሰው የማይሰጠው ፍጹም ሰላም ነውና ሁሉ ከእርሱ ከሆነ ከእግዚአብሔር ይሁንላችሁ አለ፡፡
- 1፡8 አምላኬ በኢየሱስ ክርስቶስ አመሰግናለሁ ሲል በሕይወቱ ከእግዚአብሔር ጋር ስላለው ኅብረት ጽፎልናል፡፡ ሮማውያን ክርስቲያኖች እምነታቸው ከአይሁድ ተጽዕኖ ነጻ መውጣት የሚያስፈልገው ቢሆንም ወቀሳን ሳያስቀድም አስቀድሞ በማመስገን እምነታችሁ በዓለም ሁሉ ተሰማች በማለት እግዚአብሔርን አመሰገነ - መልካም ነገር ሁሉ ከርሱ ከእግዚአብሔር ነውና፡፡
- ወደ እግዚአብሔር ሥጋውን ካልበላን ደሙን ካልጠጣን መቅረብ አይቻልም አለን፡፡
- 1፡9 እውነተኛ አባት፣ እረኛ፣ ካህን ያለማቋረጥ ስለ ሕዝቡ ይጸልያልና ቅዱስ ጳውሎስም ይህንኑ ስለማድረጉ እግዚአብሔር ምስክሬ ነው አለ፡፡ *ቀዳ ሳሙ 12፡23* የሚያስታውሰንም ይህን ነው፡፡
- እግዚአብሔር ቀንና ሌሊት ወደርሱ ሲጸልይ ይሰማው ነበርና ምስክሩ ነውና ስታመልኩት በእውነትና በመንፈስ አምልኩት እንጂ በከንፈር አይሁን አለ፡፡ *ማቴ 15፡8፡፡*
- 1፡10 የሮምን ሰዎች ለመጎብኘት ቢሻም ከጉዞው በፊት በመጸለይ ከውሳኔያችንና ድርጊታችን በፊት እንድንጸልይ እግዚአብሔርን እንድንጠይቅ በማስተማር ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ወደ እናንተ ብመጣ አገልግሎቴ ከንቱ ይሆናል በማለት ከራሱ ፈቃድ በፊት የእግዚአብሔርን ፈቃድ አስቀደመ፡፡
- 1፡11 የእግዚአብሔር አገልጋይ ልቡ ለመርዳት፣ ለማስተካከል፣ ሰውን ወደ ትክክለኛው መንገድ ለመምራት ይናፍቃልና ስለዚህ ከመንፈስቅዱስ የሆነውን ስጦታ ሊያካፍላቸው ወደደ፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 1

**ወደ ሮሜ ሰዎች - ምዕራፍ 1**

- እርሱ የሚሰጣቸው ከመንፈስቅዱስ የሆነ ስጦታ ከአይሁድም ከሆነ በሕግ ከመመካት ከአሕዛብ ከሆነ የሥልጣን ትምክህተኝነት ስህተት ይጠብቃቸዋል፡፡
- 1፡12 እኔ ብቻ ሳልሆን እናንተም ልታግዙኝ ሁሉም ሊረዳዳ ይገባልና እኔ እናንተን ሳግዝ እናንተ ደግሞ እኔን አግዙ አለ፡፡
- ከዚሁ ጋር እምነታችሁ መሠረቱ አንድ ቢሆንም መታረም የሚገባው ነገር ግን አለው አላቸው፡፡
- 1፡13 መጸለይ መጠየቅ ብቻ ሳይሆን መሥራት ተግባርንም ገንዘብ ማድረግ ይገባል አላቸው፡፡ ጊዜው ሳይሆን ቀርቶ በሩ ከተዘጋ እስኪከፈት ጠብቄ እግዚአብሔር የተሻለ ዕቅድ ቢኖረው የሆነ ነውና፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ በሌሎች ከተሞች እንዳደረገው በሮምም ያለውን ኃላፊነት ለመወጣት የነበረው የኃላፊነት ስሜት ከፍ ያለ ነበር፡፡ ስለዚህ ጊዜው እስኪደርስ ታገሡ አለ፡፡
- 1፡14 እግዚአብሔር አደራ ስለሰጠው ሁሉም እንዲስተካከሉ ይፈልግ ነበር፡፡ ግሪኮች ወይም አይሁድ ለየራሳቸው ጥበበኞች እንደሆኑ አስበው ሌሎችን አላዋቂ አደረጉ፡፡ እርሱ ግን ጥበበኛው ማነው ሞኖችስ እነማን ናቸው? በማለት ጻፈላቸው፡፡
- 1፡15 በሮም ካለው በሥልጣንና በጉልበት የማመን ስሜት የተነሳ ማስተማር ቢከብድም በእኔ እንዳለ ችሎታ፣ ጥበብ፣ ጽንዓት … የተሰቀለውን ክርስቶስን መስበክ እንዴት ሊቀል ይችላል፤ ነገር ግን ብሞትም፣ የሚብሰውም ሁሉ ቢደረግብኝ በሮሜ ወንጌልን ለማስተማር ተዘጋጅቻለሁ አለ፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 1

**ወደ ሮሜ ሰዎች - ምዕራፍ 1**

- 1፡16 በሮም የነበረው በጉልበትና በኃይል የማሰብ ሕይወት ፈታኝ ቢሆንም ወንጌልን ፣ ይቅርታን፣ ጠላትን ይቅር ስለማለት፣ **በመስበኬ** አላፍርም፡፡ ወንጌሉ የሞራል መትሐፍ ሳይሆን ለማዳን የተዘጋጀ ኃይል ነውና አለ፡፡
- መንፈስቅዱስ ወንጌሉን ዛሬም ለእያንዳንዳችን እየገለጠ ወደ ጥቅማችን ይመራናል መጀመሪያ ለአይሁድ ከምድረ እስራኤል ቀጥሎ ለግሪክ ሰዎች በምድረ አሕዛብ የተሰበከው ለማዳን ነውና፡፡
- 1፡17 በእምነት እንጠነክራለን እምነት መንገድ ነው… ቃሉን በሕይወት በመጠበቅ ያድጋል ጻድቃንም የዳኑት በዚሁ ነው፡፡ ‹‹ጻድቅ ግን በእምነቱ በሕይወት ይኖራል፡፡›› *ዕን 2፡4፡፡* … እስከ ሞት በማመን በመቁረብ… ጽኑ አለ፡፡
- 1፡18 የሰው ልጅ ዓመፃ በዓለም ውስጥ በየጊዜው እየተስፋፋ ይገኛል፡፡ ይህም የእግዚአብሔርን ቁጣ የሚያነሳሳ ነው፡፡ እግዚአብሔር ኃጢአትን እንጂ ኃጢአተኞችን አይጠላም፡፡ ሰው የሆነው የሞተውም ለኃጢአተኞች ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ ቁጥር የነገረን ኃጢአቶች እውነት እንዳይነገር እውነት እንዳይስፋፋ እውነትን ለመከላከል የሚፈጸሙ የዓመፃ ሥራዎች ነበሩ፡፡
- እውነት ከሰው ልጆች ውድቀት በኋላ በሕገ ልቦና በሰው ሕይወት ውስጥ ቀርታ ሰው የሆነ ሁሉ እግዚአብሔርን ማወቅ የምታስችለን ናት፡፡ እውነትን በኃጢአታችን በመሸፈናችን የተነሳ ወደ ፍጹም ጨለማ እንወድቃለን፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 1

**ወደ ሮሜ ሰዎች - ምዕራፍ 1**

- ሳንሰበክ የእግዚአብሔርን መኖር በፍጥረታቱ የተነሳ ማን ፈጠራቸው? ብለን በመጠየቅ ልናውቅ እንችላለን። ይህን እውነት ከማወቅም ጋር ሥጋ የለበሰውን አምላካችንን ኢየሱስ ክርስቶስንም አምላክነት ማመን አለብን።
- ዮሴፍ ነውርን እንዳያደርግ ያበቃው ልቦናው እንጂ መምህር ወይም መጽሐፍ አልነበረም። ***ዘፍጥ 39፡8።*** ያም ሆኖ ለዮሴፍ የአምላካችን ሰው መሆን ነጻ ለመውጣቱ አስፈላጊው ነበር።
- 1፡19 አንድን ሕንጻ አይተን ከጀርባው ኢንጂነሮች ያሉ መሆናቸውን ማንም ሳይለን እንደምናስብ የእግዚአብሔርን መኖር መጻሕፍትን ሳናነብ ከፍጥረታቱ ልንረዳ እንችላለን።
- በውስጣችን ያለውን በዓመፃ ያልተከደነ እውነት ከሰማን እግዚአብሔር እንዳለ ማወቅ እንችላለን።
- 1፡20 ፈጣሪ እንጂ ፍጡር ያልሆነውን በተፈጥሮአዊው ዓይናችን ልናየው የማንችለውን እግዚአብሔርን ኀልውናው ከቀድሞ ጀምሮ እንደሆነ ዓለምን አሳልፎ የሚኖር ኃያል እንደሆነ ልናውቅ እንችላለን።
- 1፡21-28 በሮሜ የነበሩ አንዳንዶች ሰዎች እግዚአብሔር መኖሩን ቢያውቁም አላመሰገኑትም፣ አላከበሩትም፣… መኖሩን ልባቸው ቢያውቀውም አለመኖሩን ለማስረዳት ብዙ ማስረጃ ለማቅረብ ይሞክራሉ…
- እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጥረት በማድነቅ ፈንታ በሞኝነታቸውም ወደሞት አመሩ።
- በዚህ አካሄድ የሚሄዱ አዕምሮአቸው/ሐሳባቸው ያመነጨውን ክፉውን ነገር ሁሉ ሳይቀር አመኑ፤ በእምነታቸው በማደግ ምትክ ከጨለማ ወደ ጨለማ አመሩ።

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 1

**ወደ ሮሜ ሰዎች - ምዕራፍ 1**

- እውነተኛውን እግዚአብሔርን ትተው የተቀረጸውን ምስል ተክተው አምልከዋልና ሞኝነታቸው ተገለጠ፡፡
- እግዚአብሔር መኖሩን እያወቁ ሊያመልኩት ግን አልፈለጉም፡፡ … ነውር በሆነው ሥራቸውም ውጤት ወደ ወረደ ደረጃ ወደቁ…
- መንፈሳውያን በመንፈሳዊ ሕይወት ይኖራሉ…. ያላመነ ሰው በመጨረሻ እንደ እንስሳ ይሆናልና በገዛ ፍትወታቸው ወደቁ፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ የአሕዛብ ሥራቸውን ጥቂቱን እንጂ ሁሉን አልጻፈም፡፡ ሌሎቹ ጸሐፍት የጻፉትን የአሕዛብ ሥራቸውን ሁሉ ብናውቅ ፈጽመን በነፍሳችን እንሳቀቃለን፡፡ አሕዛብ ፈጣሪን ሳይሆን ፍጡርን አመለኩ፡፡
- በዚህም የተነሳ ጸጋውን ነሳቸው፡፡ እነርሱም ዓይን አውጣ ሆነው ማፈርን ሁሉ ትተው ግብረ ሰዶማውያን ሆኑ… በግኑኝነት ያልተፈቀደውን በሕግም የተወገዘውን በድፍረት ፈጸሙ፡፡
- 1:29-32 በመጨረሻም ሙሉ ለሙሉ ያለቅድስና በመኖር ወደቁ፡፡ ይህም እግዚአብሔርን ያለመታዘዝ ውጤት ምን እንደሆነ ምንም እንደሚያስከትልብን የሚያስገነዝበን ነው፡፡
- በዚያ ዘመን የነበሩ የተወለዱ ጨቅላ ሕጻናትን በቅዝቃዜ (በብርድ) ውስጥ እየጣሉ ይገድሉ ነበር፡፡
- የሚሠሩት ጥፋት፣ እግዚአብሔርም ጻድቅ ፈራጅ እንደሆነ ቢያውቁም በዓመፃቸው ገፉበት፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 1

**ወደ ሮሜ ሰዎች - ምዕራፍ 1**

- ባለው ላይ ዓመፃ ሁሉ፥ ግፍ፥ መመኘት፥ ክፋት ሞላባቸው፤ ቅናትን፥ ነፍስ መግደልን፥ ክርክርን፥ ተንኰልን፥ ክፉ ጠባይን ተሞሉ፤ የሚያሾከሹኩ፥ሐሜተኞች፥ አምላክን የሚጠሉ፥ የሚያንገላቱ፥ ትዕቢተኞች፥ ትምክህተኞች፥ ክፋትን የሚፈላለጉ፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥የማያስተውሉ፥ ውል የሚያፈርሱ፥ ፍቅር የሌላቸው፥ ምሕረት ያጡ ሆነው ተገኙ።
- እነዚህን የሚያደርጉ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም ይህን እንዲያደርጉ የሚያበረታቱ ሆኑ፤ ይህም ከሁሉም የበለጠ በደል ነው።
- እንደዚህ የሚኖሩ እነዚህ አዳኙ መድኃኒትና ድኅነት አስፈለጋቸው።
- እነዚህን ለማዳን የመጣ አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክብርና ምስጋና ይግባው። አሜን።

# ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org